**አቢራው ሲረጋ፤ የስደተኛ ቤተሰቦች ከተገናኙ በኋላ ያላቸውን የሕይወት ተሞክሮ መዳሰስ**

**የፕሮጀክት መረጃ ሉህ/ቅጽ**

ቱጌዘር ናዉ ( Together Now) ከ 2010 ጀምሮ የስደተኞች ቤተሰብን የመገናኘት ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል።

**ማን ሊሳተፍ ይችላል? (ከዚህ በታች ያሉትን ሁሉንም መመዘኛዎች ማሟላት ያስፈልግዎታል)**

● በስደተኛ ቤተሰብ የመገናኘት ቪዛ በመጠቀም የተገናኙ ቤተሰቦች ወይም ጥንዶች

● ከግንቦት 2021 በፊት እንደገና የተገናኙ ቤተሰቦች ወይም ጥንዶች

● በእንግሊዝ ቀይ መስቀል (British Red Cross) ቱጌዘር ናዉ ( Together Now) ወይም ራሳቸው ትኬት የቆረጡ ቤተሰቦች ወይም ባለትዳሮች

● ስፖንሰር አድራጊውም ሆነ መጪው የትዳር ጓደኛ መሳተፍ የሚፈልጉባቸው ቤተሰቦች ወይም ጥንዶች

● መሠረታዊ እንግሊዝኛ የመናገር ችሎታ ያላቸው ቤተሰቦች ወይም ጥንዶች። ካስፈለገ አስተርጓሚ ማቅረብ እንችል ይሆናል።

**እነማን ይሳተፋሉ?**

ከምስራቃዊ አንግሊያ ዩኒቨርሲቲ (the University of East Anglia )ተመራማሪ ከሆነችው ማሪያ አብራንችስ (Maria Abranches)ጋር በመተባበር እየሰራን ነው። ከስደተኞች እና ከስደት ጋር በተያያዙ በርካታ ፕሮጀክቶች ላይ ሰርታለች። ከሰዎች ጋር ተገናኝታ ስለ ልምዳቸው ትጠይቃቸዋለች።

ማሪያ (Maria) ኒሃያ ጃብር (Nihaya Jaber) ፣ በተባለችው ረዳት ተመራማሪ ትታገዛለች። ኒሃያ( Nihaya) አረብኛ ተናጋሪ ናት። በእንግሊዝ አገር (UK) የስደተኞች ጉዳዮች ዙሪያ ልምድ ያካበተች ናት። ማሪያን እና ኒሃያን (Maria and Nihaya)የሚረዷቸው በጎ ፈቃደኞች አሉ።

**ስለ ሰዎች ተሞክሮ እንዴት ማግኘት እንችላለን?**

ይህንን ለማድረግ ሦስት መንገዶች አሉ-

1. የእግር ጉዞ ቃለመጠይቆች፡- ይህ አብረው በእግር ለመጓዝ የሚሄዱበት እና ማሪያ እና ኒሃያ (Maria and Nihaya) የሚኖሩበትን አካባቢ ወይም ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነውን ሌላ የከተማውን አካባቢ ማሳየት የሚችሉበት ነው ። በእነዚያ አካባቢዎች ፎቶግራፍ እንዲያነሱ እና ድምጽ እንዲቀዱ ይጠየቃሉ።

2. የግለሰብ ቃለመጠይቆች፡- እዚህ ከማሪያ እና ከኒሃያ (Maria and Nihaya )(ወይንም ከአንዳቸው ጋር ብቻ) ውይይት የሚያደርጉበት ነው። ይህም የበለጠ ዝርዝር ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ እድል ይሰጣቸዋል።

3. የቡድን አውደ ጥናቶች፡- እነዚህ በምርምር ውስጥ የተሳተፉ ሌሎች ቤተሰቦችን የምታገኙባቸው ክፍለ ጊዜዎች ይሆናሉ። ስለ ፕሮጀክቱ ያላችሁን ስሜት ለማካፈል እና ስለ ጥናቱ የመጀመሪያ ግኝቶች ለመወያየት የምትችሉበት ነው።

ከፈለጋችሁ ያነሳችኋቸውን ፎቶዎች እና የቀረጻችኋቸውን ድምጾች እና ከቃለ ምልልሱ የተገኙ ታሪኮችን በመጠቀም አጭር ፊልም በጋራ መስራት ላይ ለመሳተፍ እድሉ ይኖራችኋል። ይህ አጭር ፊልም ሰዎች ስለ ስደተኞች እና ቤተሰቦቻቸው ያላቸውን አመለካከት እንዲረዱ እና እንዲቀይሩ ለመርዳት ይጠቅማል።

**እኔ ብሳተፍ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

በእነዚህ ክፍለ ጊዜዎች በአንዱ ወይም በሁሉም ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ያህል ይቆያል ብለን እንጠብቃለን። በዚህ ላይ የጉዞ ጊዜ ይኖራል። ክፍለ ጊዜዎቹን ለእርስዎ በሚመች ጊዜ እና ቀን ለማቻቸት እንሞክራለን። ፊልሙን የማጠናቀቁ የጋራ ስራ ግን ብዙ የአርትዖት ክፍለ ጊዜዎችን ስለሚያጠይቅ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል።

**ለምንድን ነው መሳተፍ ያለብኝ?**

ማንነትዎ ሳይገለጽ የእርስዎን ተሞክሮዎች አስተያየት ለመስጠት ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው። በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ የሚያካፍሉት መረጃ በስደተኛ ቤተሰብ የመገናኘት ሂደት ውስጥ ለሚሄዱ/ለሚያልፉ ሌሎች ቤተሰቦች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል ይጠቅማል።

እንዲሁም የእርስዎን ግብረ መልስ በመጠቀም ለስደተኛ ቤተሰቦች ለመሟገት እና ችግሮችን የሚፈጥሩ አንዳንድ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን ለመቃወም ይጠቅማል። እንዲሁም በአካባቢዎ ካሉ ሌሎች ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ጥሩ አጋጣሚ ይሆናል።

**ለእኔ ምን አገኝበታለሁ?**

ለመሳተፍ ክፍያ አይከፈልዎትም፣ ሆኖም ቱጌዘር ናው (Together Now ) ማንኛውንም የጉዞ ወጪዎችን ይከፍላል።

**ስለ ምን ልጠየቅ እችላለሁ?**

የትኛውን መረጃ እንደሚያካፍሉ መምረጥ ይችላሉ። እኛ የሚከተሉትን እንጠይቅዎታለን፡-

- ወደ እንግሊዝ አገር (UK) ከመምጣትዎ በፊት የነበረው ህይወትዎ ምን ይመስል ነበር ? (በአሉታዊ ገጠመኞች ላይ ምንም አይነት ዝርዝር መግለጫ መስጠት አያስፈልግዎትም)
- የቤተሰብ መገናኘቱ ሂደት ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ እንዴት ነበር?
- ቤተሰብዎ ወደ እንግሊዝ አገር (UK) ሲደርሱ ምን አስቸጋሪ/ፈታኝ ሁኔታዎች አጋጥመውዎታል?
- ከቤተሰብ መገናኘቱ በኋላ ስለ እንግሊዝ አገር (UK) ህይወት ማጋራት የሚፈልጉት ሌላ ነገር ካለ?

**ሃሳቤን ብቀይርስ?**

ለመሳተፍ ሀሳብዎን ከቀየሩ ራሰዎን በማንኛውም ጊዜ ማግለል ይችላሉ። ከዚያ በኋላ የተሰበሰበውን መረጃ እንድንሰርዝ ወይም እንድንጠቀምበት ስለመፈለግዎ እንወያያለን።

**የጥናት ሪፖርቱ ለእኔም ይደርሰኛል?**

አዎ። ይህ ጥናት ከመጠናቀቁ በፊት እንዲገመግሙት ለሚሳተፉት ሁሉ እናካፍላለን። ማንኛውም ቅጂዎች፣ ፊልሞች ወይም ምስሎችም እንዲሁ ይጋራሉ።

**በታተመው ዘገባ ውስጥ ስሜን ትጠቀማላችሁ?**

አንጠቀምም። ሁሉም ተሳታፊዎች ማንነታቸው ሳይታወቅ ሊቆዩ ይችላሉ። የእርስዎን ስም ወይም የግል ዝርዝሮችን አናትምም። አንዳንድ ፎቶግራፎችዎን (እና ፊልሙን ከኛ ጋር ለመስራት ከወሰኑ) በአገር ውስጥ ኤግዚቢሽኖች እና በኢንተርኔት/ኦንላየን ላይ ማሳየት ይቻል ይሆናል፣ በዚህ ጊዜ እርስዎ እንደ ጸሃፊያቸው መታወቅ ወይም ማንነተዎ እንዳይገለጽ መወሰን ይችላሉ።

**እንዴት ልሳተፍ እችላለሁ?**

ስለመሳተፈዎ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት የሚከተሉትን ሰዎች ማነጋገር ይችላሉ፡-

● ኤሚ ቱጌዘር ናው (Amy at Together Now) በ amy@togethernow.org.uk ወይም 07929337837

● ማሪያ በምስራቅ አንግሊያ ዩኒቨርሲቲ( Maria at University of East Anglia) በ m.abranches@uea.ac.uk ወይም 07506235126

**ይህ የመረጃ ሉህ/ቅጽ እርስዎ የሚያቆዩት ነው።**

**የተሳታፊ ስምምነት ቅጽ (ለተመራማሪው የመጀመሪያ ቅጂ ይሰጥ)**

በዚህ የምርምር ጥናት ውስጥ መሳተፍ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ ጥናት ላይ ለመሳተፍ ፍቃድ ከሰጡን፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት እንደተስማሙ እየነገሩን ነው፦

✔ ያነበቡትን ተረድተዋል።

✔ ከዚህ በታች በተዘረዘረው የምርምር ጥናት ለመሳተፍ ተስማምተዋል።

✔ እንደተገለጸው የእርስዎን የግል መረጃ እንድንጠቀምበት ተስማምተዋል።

✔ ለማቆየት የተሣታፊ መረጃ ሉህ/ፎርም ቅጂ ደርሶዎታል።

እኔ፣ ............................................... ................................ [ሙሉ ስም]፣ በዚህ የምርምር ጥናት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ነኝ።

**ፈቃዴን ስሰጥም እንደሚከተለው እገልጻለሁ፦**

-የጥናቱ ዓላማ፣ ምን እንዳደርግ እንደሚጠየቅ፣ እና ማንኛቸውም አደጋዎች/ጥቅሞች ተረድቻለሁ።

- በሰነድነት ላስቀምጠው የምችለውን የተሳታፊ መረጃ ወረቀት አንብቤአለሁ እና በጥናቱ መሳተፍ ከፈለግኩ ስለሚኖረኝ ተሳትፎ ከተመራማሪዎቹ ጋር መወያየት ችያለሁ።

- ተመራማሪዎቹ ስለ ጥናቱ ጥያቄዎቼን መለሰውልኛል በመልሶቹም ደስተኛ ነኝ።

- በዚህ ጥናት ውስጥ መገኘቴ ሙሉ በሙሉ በፈቃዴ እንደሆነ እና ካልፈለግኩ መሳተፍ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ። በጥናቱ የመሳተፍ/አለመሳተፌ ውሳኔ ከተመራማሪዎቹ ወይም በምስራቅ አንገሊያ ዩኒቨርስቲ (University of East Anglia) ውስጥ ካሉት ተመራማሪዎች ጋር ያለኝን ግንኙነት አሁንም ሆነ ወደፊት ተጽዕኖ አያሳድርበትም።

ለመቀጠል ካልፈለግኩ ተሳትፎዬን ላቋርጥ እንደምችል ተረድቻለሁ፣ እና ካልፈቀድኩ በስተቀር፣ ማንኛውም ቅጂዎች ይሰረዛሉ እና የቀረበው መረጃም በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ እንደማይካተት ተረድቻለሁ። እንዲሁም መልስ መስጠት የማልፈልገውን ማንኛውንም ጥያቄ አለመመለስ እንደምችል ተረድቻለሁ።

- የዚህ ጥናት ውጤት ሊታተም እንደሚችል ተረድቻለሁ ነገር ግን የትኛውም ህትመቶች ስሜን ወይም ማንኛቸውም መለያ መረጃዎችን አይይዙም።

- በዚህ ፕሮጀክት ሂደት ውስጥ ስለ እኔ የተሰበሰቡ የግል መረጃዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚቀመጡ እና ለተስማማሁባቸው ዓላማዎች ብቻ እንደሚውሉ ተረድቻለሁ። በሕግ ከተደነገገው በስተቀር ስለእኔ ያለኝ መረጃ ለሌሎች የሚገለጠው/የሚሰጠው በእኔ ፈቃድ ብቻ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እንዲደረጉ እስማማለሁ/አልስማማም፡-**

ድምጽ መቅዳት አዎ □ አይ □

ቪዲዮ መቅረጽ አዎ □ አይ □

የሚወሰዱ ማስታወሻዎች አዎ □ አይ □

ፎቶግራፎች አዎ □ አይ □

የድምጽ፣ የቪድዮና የማስታወሻ ግልባጮችን መገምገም አዎ □ አይ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለምሁራዊ እና ትምህርታዊ ዓላማዎች እንዲቀርቡ በማህደር ውስጥ ይቀመጣሉ፣ ነገር ግን መረጃው ስሜን ወይም ስለ እኔ ምንም መለያ መረጃ አይይዝም።

መረጃዎቹ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚቀመጡ አዎ □ አይ □

በዚህ ጥናት አጠቃላይ ግኝቶች ላይ አስተያየት መስጠት ይፈልጋሉ? አዎ □ አይ □

መልሰዎ **አዎ** ከሆነ፣ እባክዎን የመረጡትን አስተያየት መስጫ መንገድና እና አድራሻ ያመልክቱ።

ፖስታ፡ ____________________________________________________________

ኢሜል፡ ________________________________________________

ፊርማ................................................ .................

ስም................................................ .................

ቀን................................................ .................

## የተሳታፊ ስምምነት ቅጽ (ሁለተኛ ቅጂ ለተሳታፊ ይሰጥ)

በዚህ የምርምር ጥናት ውስጥ መሳተፍ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ ጥናት ላይ ለመሳተፍ ፍቃድ ከሰጡን፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት እንደተስማሙ እየነገሩን ነው፡-

✔ ያነበቡትን ተረድተዋል።

✔ ከዚህ በታች በተዘረዘረው የምርምር ጥናት ለመሳተፍ ተስማምተዋል።

✔ እንደተገለጸው የእርስዎን የግል መረጃ እንድንጠቀምበት ተስማምተዋል።

✔ ለማቆየት የተሣታፊ መረጃ ሉህ/ፎርም ቅጂ ደርሶዎታል።

እኔ፣ ............................................... ................................ [ሙሉ ስም]፣ በዚህ የምርምር ጥናት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ነኝ።

ፈቃዴን ስሰጥም እንደሚከተለው እገልጻለሁ፡-

የጥናቱ ዓላማ፣ ምን እንዳደርግ እንደሚጠየቅ፣ እና ማንኛቸውም አደጋዎች/ጥቅሞች ተረድቻለሁ።

- በሰነድነት ላስቀምጠው የምችለውን የተሳታፊ መረጃ ወረቀት አንብቤአለሁ እና በጥናቱ መሳተፍ ከፈለግኩ ስለሚኖረኝ ተሳትፎ ከተመራማሪዎቹ ጋር መወያየት ችያለሁ።

- ተመራማሪዎቹ ስለ ጥናቱ ጥያቄዎቼን መለሰውልኛል በመልሶቹም ደስተኛ ነኝ።

- በዚህ ጥናት ውስጥ መገኘቴ ሙሉ በሙሉ በፈቃዴ እንደሆነ እና ካልፈለግኩ መሳተፍ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ። በጥናቱ የመሳተፍ/አለመሳተፌ ውሳኔ ከተመራማሪዎቹ ወይም በምስራቅ አንግሊያ ዩኒቨርስቲ (University of East Anglia) ውስጥ ካሉት ተመራማሪዎች ጋር ያለኝን ግንኙነት አሁንም ሆነ ወደፊት ተጽዕኖ አያሳድርበትም።

ለመቀጠል ካልፈለግኩ ተሳትፎዬን ላቋርጥ እንደምችል ተረድቻለሁ፣ እና ካልፈቀድኩ በስተቀር፣ ማንኛውም ቅጂዎች ይሰረዛሉ እና የቀረበው መረጃም በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ እንደማይካተት ተረድቻለሁ። እንዲሁም መልስ መስጠት የማልፈልገውን ማንኛውንም ጥያቄ አለመመለስ እንደምችል ተረድቻለሁ።

- የዚህ ጥናት ውጤት ሊታተም እንደሚችል ተረድቻለሁ ነገር ግን የትኛውም ህትመቶች ስሜን ወይም ማንኛቸውም መለያ መረጃዎችን አይይዙም።

- በዚህ ፕሮጀክት ሂደት ውስጥ ስለ እኔ የተሰበሰቡ የግል መረጃዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚቀመጡ እና ለተስማማሁባቸው ዓላማዎች ብቻ እንደሚውሉ ተረድቻለሁ። በሕግ ከተደነገገው በስተቀር ስለእኔ ያለኝ መረጃ ለሌሎች የሚገለጠው/የሚሰጠው በእኔ ፈቃድ ብቻ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እንዲደረጉ እስማማለሁ/አልስማማም፡-**

ድምጽ መቅዳት አዎ □ አይ □

ቪዲዮ መቅረጽ አዎ □ አይ □

የሚወሰዱ ማስታወሻዎች አዎ □ አይ □

ፎቶግራፎች አዎ □ አይ □

የድምጽ፣ የቪድዮና የማስታወሻ ግልባጮችን መገምገም አዎ □ አይ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለምሁራዊ እና ትምህርታዊ ዓላማዎች እንዲቀርቡ በማህደር ውስጥ ይቀመጣሉ፣ ነገር ግን መረጃው ስሜን ወይም ስለ እኔ ምንም መለያ መረጃ አይይዝም።

መረጃዎቹ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚቀመጡ አዎ □ አይ □

በዚህ ጥናት አጠቃላይ ግኝቶች ላይ አስተያየት መስጠት ይፈልጋሉ? አዎ □ አይ □

መልሰዎ አዎ ከሆነ፣ እባክዎን የመረጡትን አስተያየት መስጫ መንገድና እና አድራሻ ያመልክቱ።

ፖስታ፡ ____________________________________________________________

ኢሜል፡ ________________________________________________

ፊርማ................................................ .................

ስም................................................ .................

ቀን................................................ .................